# እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2020 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፉት የፌብርዋሪ ወር በመጀመሪያዉ እና ሁለተኛዉ አስር ቀናት ወደ አገራች ይገባ የነበረዉ ዕረጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ ገፅታ ነበረዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በሌላ በኩል በደቡባዊ ንፍቀ ክብብ በተለይም በማዳጋስካር አካባቢ የተፈጠረዉ ዝቅተኛ የአየር ግፊት በመጠናከሩ በመጀመሪያዉ እና ሁለተኛዉ አስር ቀናት ወደ አገራችን ይገባ የነበረዉ ዕርጥበት አንፃራዊ በሆነ መልኩ በመዳከሙ በሶስተኛዉ አስር ቀናት ላይ ከደቡብ እና ከደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በስተቀር ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ፀሃያማ እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት መጠን በተለይም በአንዳንድ የአገሪቱ ቆላማ ስፍራዎች ላይ አንፃራዊ በሆነ መልኩ እንደጨመረ የተሰበሰቡ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በምስራቅ አማራ እና አጎራባች በሆኑ የአፋር እንዲሁም ደቡብ ትግራይ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ የተቀሩት የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ፀሃያማ እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ቆይተዋል፡፡

ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በጅማ እና ኢሉአባቦራ፣ በምዕራብ ሸዋ፣ በምስራቅ እና ሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በጥቂት የሰሜን ሸዋ፣ በአርሲና ምዕራብ ሐረርጌ፣ በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ በዋግህምራ፣ በደቡብ ትግራይና የአፋር ክልል ዞን 05 ላይ ከ5-86 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-14 ቀናት ያህል ነበራቸዉ፡፡


ባለፈዉ የፌብርዋሪ ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በጥቂት የቦረና፣ ኢሉአባራ እና ጅማ፣ በመተከል፣ ምዕራብ ጎጃም እና ምስራቅ ጎጃም እንዲሁም ደቡብ ጎንደር ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፣ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል፡፡

ባለፈዉ የማርች ወር ዕርጥበታማዉ የአየር ሁኔታ በሁለተኛዉ አስር ቀናት እና በሶስተኛ አስር ቀናት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ላይ የተሻለ ገፅታ ነበረዉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ዝናቡ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ በበልግ አብቃይ አካባቢዎች ላይ የተሻለ እንደ ነበረ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የማርች ወር በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል፣ በደቡብ፣ በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በምዕራብ ኦሮሚያ፣ በምስራቅ አማራ፣ በአፋር፣ በደቡብ ትግራይ፣ በጋምቤላና ሱማሌ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይም ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡


ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ በአርሲና ባሌ፣ በጉጂ፣ ቦረና፣ በምዕራብ ሐረርጌ፣ በአፋር ክልል ዞን 03ና 01፣ በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች ላይ ከ55-287 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ10-23 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በሱማሌና ጋምቤላ ክልሎች ዞኖች ላይ፣ በወለጋ ዞኖች፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ወሎና ደቡብ ትግራይ ዞኖች ላይ ከ5-55 ሚሜ የሚደርስ ከ5 ቀናት በታች ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከከፋና ሸካ ዞኖች በስተቀር በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ በምዕራብ ወለጋ፣ በአርሲ፣ ጉጂና ቦረና፣ በደቡብ ወሎ፣ በአፋር ዞን 01ና 03፣ በሲቲ፣ በፋፈንና ሊበን ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል፡፡

በአጠቃላይ የበልግ ወቅት አጋማሽ ጊዜን በሚሸፍኑት የፌብርዋሪ እና የማርች ወራት የዘነበዉ የዝናብ መጠን እየተሻሻለ እንደነበረ እና ከመደበኛዉ ጋርም ሲነፃፀር በጉጂና ቦረና፣ በምዕራብ ወለጋና ጂማ፣ ከሞላጎደል በሁሉም የሸዋና በጥቂት የባሌ ዞኖች፣ በምስራቅ ጎጃምና ደቡብ ወሎ፣ በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ዞኖች፣ በሊበን፣ ሲቲና ፋፈና፣ በአፋር ክልል ዞን 1ና 3 ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ በተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-ማርች 31/2020 የነበረዉ የዝናብ መጠን በሚሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ. ከፌብርዋሪ 1-ማርች 31/2020 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛ ጋር ሲነፃፀር

## እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2020 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና የስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፈው የፌብርዋሪ ወር 2020 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ሲገመገም በመጀመሪያዎቹ እና በሁለተኛዎቹ አስር ቀናት በተለይም የበልግ ሰብል አብቃይ በሆኑት አካባቢዎች የተሻለ የእርጥበት ገጽታ እንደነበራቸው የተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚህም ጋር ተያይዞ በተወሰኑ በሰሜን፤ በሰሜን ምስራቅ፤ በምስራቅ፤ በመካከለኛው፤ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ አንዳንድ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት እንደነበራቸው መረጃዎች አመልክተዋል። ሆኖም ግን በሶስተኛው አስር ቀናት ላይ ከደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች በስተቀር ሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ

እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ የተስተዋለ ቢሆንም፣ በወሩ የተገኘው እርጥበት የበልግ ሰብል በስፋት አምራች ለሆኑት ለደቡብ ምእራብ አካባቢዎችም ሆነ ለሰሜን ምስራቅ እና ለመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ ከፍተኛ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ከነበረው አስተዋፅዎ ጎን ለጎን ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ሚና ነበረው። በሌላ በኩል በተለይም በቆላማ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለው ከፍተኛ ሙቀት አፈር ውስጥ የሚገኘውን እርጥበት እንዲቀንስ ከማድረግም ሆነ ከአንስሳት ጤንነትና አመጋገብ አንፃር የተወሰነ አሉታዊ ጎን ነበረው ።


ማርች ሁለተኛዉ የበልግ ወር ሲሆን በዚህ ጊዜ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት በአብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ በሆኑ አካባበቢዎች የተስፋፋ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በወቅቱ እየተከናወኑ ለነበሩት የግብርና ስራ እንቅስቃሴዎች ማለትም ማሳ ለማዘጋጀት፣ ዘር ለመዝራትም ሆነ የመጠጥ ውኃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት ላይ የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ በአጠቃላይ በወሩ የተገኘው እርጥበት አስቀድመው ለተዘሩ የበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት አዎንታዊ ሚና የነበረው ሲሆን፣ በተጨማሪም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለሚዘሩ አካባቢዎች አስቀድመው የማሳ ዝግጅት እንዲያከናውኑና የተሟላ ዝግጅት ለማድርግ ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተገኘው እርጥበት በአካባቢዎቹ ለሚኖሩት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ዉሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡

በአጠቃላይ እ.ኤ.አ 2020 ባለፉት የፌብሪዋሪና የማርች ሁለት የበልግ ወራት በእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ሁኔታ ሰንመለከት በተለይም በፌብሪዋሪ ከመጀመሪያው አስር ቀናት ጀምሮ አብዛኛው የበልግ አብቃይና ተጠቃሚ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እረጥበት የነበራቸዉ ሲሆን በሶስተኛዉ አስር ቀናት በተወሰነ መልኩ የቀነሰበት ሁኔታ ነበር፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለዘር እና ለማሳ ዝግጅት የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ በቡቃያ እና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ነገር ግን በፌብርዋሪ ወር በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ እና ደቡብ ምስራቅ በልግ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ከመዳከሙ ጋር የነበረዉ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ለግብርናዉ እንቅስቃሴ በአርሶ አደሩ እና በአርብቶ አደሩ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የነበረዉ ቢሆንም በማርች ወር ላይ የነበረዉ በልግ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰዉ የእርጥበት ሁኔታ

ለግብርናዉ እንቅስቀሴ አወንታዊ ሚና ነበርው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በተለይም በአንዳንድ የሀገሪቱ ቆላማ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ጨምሮ የተስተዋለ ነበር፡፡




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ፌብርዋሪ 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ማርች 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ

## <u>እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ ማርች 31/2020 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>


እ.ኤ.አ 1-29 ፊብሪዋሪ 2020 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ የነበራቸው ተፋሰሶች በጥቂት የታችኛዉ አባይ፣ የመካከለኛዉና የታችኛዉ ኦሞ ጊቤ እና ስምጥ ሸለቆ ሲሆኑ፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅ እስከ ከፊል ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ ተፅዕኖ ስር ነበሩ፡፡

እ.ኤ.አ 1-31 ማርች 2020 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የነበራቸው የላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ፣ የመካከለኛዉ አባይ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ ገናሌ ዳዋ፣ አዋሽ፣ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ነበሩ፡፡ በሌላ በኩል የላይኛዉና የመካከለኛዉ አባይ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ የላይኛዉ ባሮ አኮቦ እና በጥቂት የላይኛዉ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው ኦጋዴን፣ ተከዜ፣ አፋር ደናክል፣ የታችኛው

ዋቢሸበሌ፣ አዋሽ፣ ገናሌዳዋ፣ አባይ እና ባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸዉ ነበር።



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ፌብሪዋሪ 2020 የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ማርች2020 የነበረው የእርጥበት

# እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1/2020 እስከ ሜይ 31/ 2020 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኤፕሪል ወር የበልግ ወቅት የዝናብ ሥርጭትና መጠን በተለይም የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚጠናከርበትና የሚስፋፋበት ጊዜ ከመሆኑ አንፃር ከቀዳሚዎቹ የበልግ ወራት በአማካይ ከዓመታዊዉ የዝናብ መጠን የተሻለ ድርሻ አለዉ። በሜይ ወር ደግሞ የዝናቡ ሥርጭት ከደቡብና ከደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀስ በቀስ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ ወደ ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየተስፋፋ ይሄዳል።

በመጪዎቹ ሁለት የበልግ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ አብዛኛው ክፍል የባህር ወለል ሙቀት በመደበኛዉ ላይ እንደሚገኝ የሚስተዋል ሲሆን፤ በቀሪዎቹ ሁለት የበልግ ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት በተመሳሳይ ከመደበኛው ጋር በተቀራረበ (ENSO-neutral) ሁኔታ ቀጣይ የመሆን እድሉ እስከ 65% ሊደርስ እንደሚችልና እንዲሁም የህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት መደበኛው (Neutral IOD) ሆኖ እንደሚቀጥል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አሁን ከሚስተዋለውና ለመጪዎቹ ሁለት ወራት ከተተነበዩ የባህር ወለል ሙቀትና የከባቢ አየር ሁኔታዎች በመነሳት በመጪዉ ሁለት ወራት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ

ክስተቶች ከቀዳሚዎቹ ወራት አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸዉ የሚጠበቅ ቢሆንም በወሩ ውስጥ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ደረቅ የአየር ሁኔታ ሊዘወተሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል። በአጠቃላይ በመጪዎቹ ሁለት ወራት በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ወቅታዊው ዝናብ ከሞላ ጎደል የተሻለ ጥንካሬ እንደሚኖረው የሚጠበቅ ሲሆን በተለይም በሜይ ወር በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት የሚያገኙ ሲሆን የሚኖረውም ዝናብ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ እንደሚሆን ይጠበቃል።

በአጠቃላይ በኤፕሪል ወር የሚጠበቀዉ የወቅቱ የዝናብ ሁኔታ በተመለከተ ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጂማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ምሥራቅ ሸዋ፣ አዲስ አበባ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲና ባሌ፣ ቦረናና ጉጂ፣ ድሬዳዋና ሀረሪ፣ □ጋምቤላ ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ እንዲሁም ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ ጥቂት የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ከአፋር ዞን 3፣ 4 እና 5፣ ከትግራይ ክልል የመካከለኛው፣ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ ወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ ሲዳማ፣ ደቡብ ኦሞ፣ እንዲሁም የሰገን ህዝቦች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይም ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በጥቂት ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊጥል ይችላል። ከዚህም ሌላ በጥቂት የሶማሌ ክልል ዞኖች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።

## <u>እ.ኤ.አ ከአፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2020 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በግብርና ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በመጪዎቹ ሁለት ወራት (አፕሪል እና ሜይ) በተሰጠው ትንበያ መሰረት ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸውና ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እንደሚሆን እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በጣም እርጥበታማ ሁኔታ (Humid condition) ሊኖር እንደሚችል የሚጠበቅ ሲሆን፤ ለበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት፤ ለረዥም ጊዜ የመኸር ሰብሎች ለዘር እና ለማሳ ዝግጅት አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል። በተጨማሪም በወራቶቹ ውስጥ ደራቃማ ቀናት ሊዘወተሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለው የኤፕሪል እና የሜይ ወራት በትንበያው ላይ ለተጠቀሱት የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር የሚጠበቅ ሲሆን፣ ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያ ደረጃ ላሉም ሆነ ለቋሚ ሰብሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ጥሩ አስተዋጽኦ ከመኖሩም በላይ ከአፕሪል ጀምሮ ለሚዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችን ለመዝራትም ሆነ በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የሚጠበቅ በመሆኑ አርሶ አደሮች ከወዲሁ ዝግጅት ሊያደረጉ ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚጠበቀው እርጥበት ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አረብቶ አደር አካባቢዎች ለመጠጥ ውኃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው በጣም እርጥበታማ ሁኔታ ጋር በተያያዘ በተለይ ረባዳማ፣ ውሃ ገብ እና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃውን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ ተገቢው ትኩረት ተደርጎ ውሃውን በቀላሉ ማጠንፈፍ በሚችሉበት መንገድ የሚዘጋጁበት ሁኔታ ቢመቻች ሊደርስ የሚችለውን ችግር መቀነስ ያስችላል። እንዲሁም ለዘር የተዘጋጁ ማሳዎች በጎርፍ እንዳይጠረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎች መወሰድ የሚገባ ቢሆንም፤ በመካከል ለሚገጥሙ ደረቅ ሰሞናት አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ውኃን የመሰብሰብና የማጠራቀም ተግባራት ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል እርጥበት አጠርና ከፍተኛ የውኃ ትነት ያለባቸው አካባቢዎች የውኃን ብክነትን ለመከላከል የሚያስችሉ ዘዴዎችን ሊተገብሩ ይገባል፡፡ በሌላም በኩል ከእርጥበትና ከደረቅ ሰሞናት መፈራረቅ ጋር በተያያዘ አላስፈላጊ አረሞችና ሰብሎችን የሚያጠቁ ተባዮች ሊከሰቱ ስለሚችሉ በንቃት መከታተልና አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅትና ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

## እ.ኤ.አ ከአፕሪል 1 እስከ ሜይ 31/2020 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በተሰጠው ትንበያ መሰረት በኤፕሪል ወር 2020 ብዙዎቹ የበልግ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እነዚህ ተፋሰሶች ዝናብ እንደሚያገኙና በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው አባይ፣ተከዜ እና እንዲሁም የላይኛው ዋቢሸበሌና አፋርደናከል ተፋሰሶች ላይ ከመጠኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡በአንዳንድ

ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ወራጅ ውሃ እንዲኖር አስተዋፆ ስለሚያደረግ ለውሃ ሃብት የጎላ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ኤፕሪል ወር የተሻለ የዝናብ መጠን የሚገኝበት የበልግ ወቅት በመሆኑ የውሃ እጥረት የሚስተዋልባቸው ተፋሰሶች ላይ የተለያየ የዝናብ ውሃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ውሃ ለመያዝ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን፡፡

በሚቀጥለው በሜይ ወር 2020 ከበልግ ዝናብ ተጠቃሚ ከሆኑት ተፋሰሶች በተጨማሪ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በስሜንና ደቡብ ምስራቅ የአገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ዝናብ እየተስፋፋ እንደሚሄድ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ስምጥሸለቆ፣ የላይኛዉ አዋሽ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ አባይ፣ ተከዜ፣ ገናሌዳዋ እንዲሁም የላይኛውና መካከለኛው ዋቢሸበሌና የላይኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ አዋሽ፣ ገናሌዳዋ፣ በአብዛኛው ኦጋዴን፣ የታችኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ እና የአፋርደናከል ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ይጠበቃል፡፡ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የተጠቆመ ሲሆን ይህም ሁኔታ በአዎንታዊ ጎኑ የወራጅ ውሃ መጠን እንዲጨምር አስተዋፆ ስለሚኖረው ለግድቦችና ለውሃ ማቆር ስራዎች ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል ለጎርፍ ተጋላጭ ስለሚያደርገው ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡